# ሽ ሙ ጥ

## እያሽሟጠጥን እንታገላለን…እየታገልን እናሽሟጥጣለን!!

ቁጥር 1 | እንዳመቻት የምትወጣ ነጻ ጋዜጣ | ነሃሴ 1994

# የኛ ሰው በባድመ

የሸአብያ የመስፋፋት ቅዠት ድባቅ ተመቶ የአክሱም የአድዋና የመቀሌ ኢትዮጵያዊነት መረጋገጡ ተገለጠ…የኢትዮጵያ ሆደ ሰፊነት ለአለም ሰላምና ለህግ የበላይነት ያደረገው አስተዋጽኦ መደነቁ ተሰማ……ጋጠወጡ ሸአብያ በሃይል ያልቻለውን በሰላም በመለገሱ ስለህግና ስነስርአት የማይረሳ ትምህርት መከናነቡ ታወቀ ። በተደገሰልን የዜግነት ስረዛ ጀርባ የረቀቀ ጸረ ሸአብያ ሴራ መኖሩ ተጠቆመ…

(አዲስ አበባ ሽዜናአ ነሃሴ 1994 አ/ም) በሄግ ተሰይሞ የነበረው የድንበር ሽምግልናና የህዝብ ሽንሽና ኮሚሽን ጥቂት አልባሌ ግዛቶችን ለሸአብያ ቢያስረክብም ብያኔው በመሰረቱ ሸአብያ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በሆዱ ይከጅላቸው የነበሩትን አክሱምን፣ አድዋን መቀሌንና እንዲሁም አንዳንድ ሌሎች አንጡራ የኢትዮጵያ ግዛቶችን ባለመንካቱ የአስመራ መሪዎች ውስጥ ውስጡን ሲያውጠነጥኑት የነበረውን የመስፋፋት ቅዠት ድባቅ መትቶ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት መጠናቀቁን አንድ ቀንደኛ የውጭ ጉዳይ ባለስልጣን ትላንትና ማምሻውን ይፋ አድርገዋል።

ለሪፖርተራችን ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ስማቸው ግልጽ እንዳይሆን በመጠየቃቸው በደፈናው «ቀንደኛ ባለስልጣኑ » ብለን የምንጠራቸው የውጭጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ በተለይ ለሽሙጥ ዜና አገልግሎት (ሽዜናአ) በሰጡት ቃለ ምልልስ የሸአብያ አመራር በፍርድ ቤት ተከራክሮ በህጋዊና ስልጡን መንገድ እስከጠየቀ ድረስ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል የጠየቀው ሁሉ እንዲሰጠው ቁርጠኛና ሆደ ሰፊ ውሳኔ መኖሩን እያወቀ አውዳሚ ጦርነት ውስጥ የመግባቱ ሂደት የዚህን ጋጠወጥ ሃይል ጦር ጠማሽነት ያሳያል በማለት የአስመራውን አመራር እጅግ አምርረው አውግዘዋል።

ቀንደኛ ባለስልጣኑ በዚህ ቃለ ምልልሳቸው ቡሬ ላይ እንዴት ጉድ እንደሆንን፣ በነጾሮና ጉዳይ እንዴት እንደተሰራልንና ባድመን ባልተጠበቀ ሁኔታ ለመሸወድ ያበቁንን ምክንያቶች በሰፊው ያብራሩ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም የዜጎችን ኢትዮጵያዊነት መብት በግድ እየሰረዙ ወደ ኤርትራ ከማዛወሩ ሂደት በስተጀርባ የመንግስታቸው ረቂቅ የሆነ ጸረ ሸአብያ ስትራቴጂ እንዳለ ጠቁመዋል። በየትም ይኬድ በየት መጭው ጊዜ የትርምስ ይሆናል በማለት የተነበዩት ቀንደኛ ባለስልጣን በዚህ ትርምስ መንግስታቸው ከማን ወግኖ ማንን ይፋለማል የሚለው ጥያቄ ግን ለጊዜው በእንጥልጥል ያለ ጉዳይ መሆኑን በሰፊው አብራርተዋል። የቃለ ምልልሱ ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ይነበባል።

**ሸዜናአ**

የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ከተሰማ ጀምሮ የኢትዮጵያም መንግስት የኤርትራም መንግስት ( የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልሰጠ በስተቀር ከእንግዲህ በውይይቱ ወያኔና ሸአብያ ብለን የምንጠራቸው ) ሙሉ በሙሉ አሸነፍን እያሉ ነው። ድሮም ጦርነቱ የተነሳው ሸአብያ በኢትዮጵያ አስተዳደር ስር የነበሩ ግዛቶችን ወረረ ተብሎ ነበር። ብዙ ደም ፈሶ እነዚህን ግዛቶች በግድ አስለቅቀን ያዝን። አሁን ደግሞ መልሰን አስከብናቸው። ኢትዮጵያ ከዛሬ አራት አመት ይልቅ ዛሬ ጠባለች። ከኤርትራ ተቆርሶ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ስንዝር መሬት የለም። ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ድል አደረገች ያላችሁት ታዲያ የቱ ላይ ነው?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

አለመግባባት ነው። የኢትዮጵያ ድል ወይም ሽንፈት የሚለካው የግዛቷን ስፋትና ጥበት ለመለካት ቀላድ እየተጣለ አይደለም። ልብ ብለህ ተመልከት! እኛም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩም «ሰላምና የህግ የበላይነት ሙሉ በሙሉ አሸነፉ» ነው ያልነው። ጋጠወጥነትና ስርአተ አልበኛነት ድባቅ ተመቱ ነው የተባለው። ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ድል ያደረገችው በዚህ ምክንያት ነው። የሚያዝያ አምስቱን የሚኒስትሮች ምክር ቤት መግለጫ ተመልከት። እጠቅሳለሁ « ሰላም በጦርነት ላይ፣ ህግና ስነስርአት በህገወጥነትና በስርአተ አልበኝነት ላይ ድል ተቀዳጁ…አገራችን የተጎናጸፈችው ወሳኙ ድል ይህ እንደሆነ ትገነዘባለች» ይላል። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩም በሸአብያ ላይ ኢትዮጵያ ስለተጎናጸፈችው ድል ምንነት ሲያስረዱ ሚያዝያ አስር ይፋ በሆነው ቃለ ምልልስ ላይ ይህንኑ አረጋግጠዋል። እጠቅሳለሁ፣ « የአለም ህብረተሰብ የተቀበለውን የህግ የበላይነት መርህ መልሶ ያረጋገጠ በመሆኑ ዋንኛው ድላችን ይህ ነው እንላለን።»

ድሮስ ቢሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆቹን የሰዋው ለምን ሆነና?? ጋጠወጥነትንና ስርአተ አልበኝነትን አሻፈረኝ ብሎ እኮ ነበር የተሰዋው! ግንባር ቀደም ድርጅታችን ኢህአዴግ ሚያዝያ ስምንት ያወጣውን መግለጫ ተመልከት። አሁንም እጠቅሳለሁ « የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆቹን እየመረቀ የሸኘውና በሺዎች የሚቆጠሩ ልጆቹን ክቡር መስዋእትነት በጸጋ የተቀበለው ከምንም ነገር በላይ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ነበር።» ብሎ በግልጽና በትክክል አስቀምጦታል። የግዛት ስፋትና ጥበትን ከቁም ነገር ጥፎ ያነሳው ማንም የለም።

ኢትዮጵያ ጦርነቱን አሸንፋለች። ግን ጦርነቱ ሲጀመር ከነበራት ግዛቶች የተወሰኑት ተወስደውባታል። ጦር ጠማሹ ሸአብያ ግን በጦርነቱ ተሸንፏል። ግን ደግሞ ጦርነቱ ሲጀመር ከነበረው መሬት ዛሬ ይበልጥ ይዟል። ታዲያ የኛ ድልስ ሆነ የሸአብያ ሽንፈት የት ላይ ነው? መነሻ ነጥባችን ኢትዮጵያ የሰውም ባለመፈለግ የራሷንም ባለማስነካት የታወቀች አገር ነች የሚለው ነጥብ ነው።

ኢትዮጵያ የሰው አትፈልግም። ስለዚህ በዚህ በተፈጠረው ግርግር አሳብባ፣ ጦርነት አሸንፌያለሁ ብላ የሰው ይሰጠኝ አላለችም። የሰው ስለማትፈልግ ስንዝር የኤርትራ መሬት አልጠየቀችም። ስንዝር የኤርትራ መሬትም አላገኘችም። በወታደራዊ ድል ተሳክራ የጠየቀችው ነገር የለም። ይህ አይነቱ ራስን የመቆጣጠር ችሎታ ራሱን የቻለ አንድ ወሳኝና ታላቅ ድል ነው።

ኢትዮጵያ የራሷንም አታስነካም። ይህ ምን ማለት ነው? በጋጠወጥነት ዘው ብሎ በእብሪት ተነሳስቶ አገር ልውሰድ የሚል ሃይል ከመጣ ትከላከላለች፤ ድልም ታደርጋለች ማለት ነው። በሰላምና በስልጡን ዘዴ በጥሞናና በስነስርአት ስትጠየቅ ግን ይኸ ላይሰራ እንደሚችል ትኩረቷ ሜትር ካሬ ላይ ሳይሆን ስነስርአት ጨዋነትና የህግ የበላይነት ላይ እንደሆነ ለዚህም ሲባል እንኳን የጂን የአፏን ለመልቀቅ ወደኋላ እንደማትል በታሪኳ ደጋግማ አሳይታለች ።

የኤርትራን የራሷን አፈጣጠር ሁኔታ ተመልከት። ጣልያን በስነስርአት ጠየቀ። በውል በህግ ተሰጠው።

እብሪት ከጀለውና ድንበር ጥሶ መጣ። አድዋ ላይ የሆነውን ሆነ። ድባቅ ከተመታ በኋላ ትምህርት ቀሰመ። ጨመተ። በስነስርአት መጠየቁ ብቻ የሚያዋጣ መሆኑን ተገነዘበ ። በስነስርአት ተለማመጠ። ዛሬ በዘሄግ የተዳኘንባቸው ውሎች በሙሉ ከአድዋው አሸብራቂ ድል በኋላ በስነ ስርአት የተፈረሙ ውሎች ናቸው። ተቃዋሚ ተብየው ምንም ነገር የማይገባው ስለሆነ እነዚህ ውሎች ኢትዮጵያ ደካማ በሆነችበት ሁኔታ በግድ የተጫኑባት፣ ለሃገራችን ጥቅም ጎጂ ሰነዶች ነበሩ እያለ ታሪክን ለማጣመም ይከጅላል። በበኩሌ እንዲህ አይነቱን «ሳትወድ ተገዳ» የሚል አቀራረብ ለሃያሏና ስደጓ እናት አገራችን እንደስድብ እቆጥረዋለሁ።

እነዚህ ውሎች የተፈረሙት ጣልያኖች ከአድዋው ውርደት ገና ነፍስ ያልዘራባቸው ደካሞች ፣ኢትዮጵያ ደግሞ ጠንካራ ሆና በምትገኝበት የታሪክ ወቅት ነው። ይኸ ደግሞ ክቡር አምባሳደር ፍስሃ ይመርና ክቡር አቶ ሰይፈስላሴ ለማ ሚያዝያ ዘጠኝ ቀን በሰጡት ቃለምልልስ ተረጋግጧል። እጠቅሳለሁ፣ « ውሎቹ በአድዋ ድል ማግስት የተደረጉ ውሎች ስለነበሩና ኢትዮጵያ በጠንካራ ሁኔታ ስለነበረች የተደራደረችው ከጠንካራ አቋም ነው። ይዘታቸውንም ስንመለከት ደካማነትን አያንጸባርቅም። ኢትዮጵያን የሚጎዱ ውሎች ነበሩ ብሎ መገመት ትክክል አይደለም» በማለት በማያሻማ ሁኔታ አብራርተውታል።

ዛሬም ከባድመ ድል በኋላ የሚታየው ይኸው ነው። ታሪክ ራሷን ትደግማለች እንደሚሉት መሆኑ ነው። ሸአብያ ጦር ጠማሽና የጋጠወጥ ባለጌዎች ጥርቃሞ ስለሆነ ማንንም ሳያስፈቅድ ዘው ብሎ አገር ያዘ። «ስነስርአት የህግ የበላይነት!» አልነው። አልሰማም። አይቀጡ ቅጣት ተቀጣ። ልክ በአድዋ ድል ማግስት በጣልያኖች ላይ እንደተደረገው እዚህም አንድ እግሩ መቃብር ገብቶ የነበረው የሸአብያ አመራር ከሽንፈቱ ገና ነፍስ ሳይዘራበት በቅልጥፍና ተንቀሳቅሰን ነገሩ በህግ የበላይነትእንዲጠናቀቅ አደረግን። ቢጋጠወጥነት የከጀለውን መሬት በሰላም፣በፍርድ እንዳይነፈገው የተቻለው ሁሉ ተሞከረ። እንደ ሸአብያ አይነት ጦር ጠማሽ ሃይል ቅንጣት ነገርም ብትሆን በሰላም ማግኘትን እንደ ትልቅ ውርደትና ሽንፈት እንደሚቆጥረው አትርሳ። የኛ ድልና የነሱ ሽንፈት በዚህ መልክ አይረሱ ትምህርት መከናነቡ ነው።

የኮሚሽኑን ውሳኔ ሁለታችንም ከወዲሁ እንቀበላለን ብለን ቃል ገብተናል። መሬት ቢወሰድብንም ኢትዮጵያ ቃሏን አክባሪ የሰላም ሃይል ስለሆነች በዚህ የተነሳ ጦር አትመዝም። እስቲ የኢትዮጵያ ህዝብ አንዲት ሰከንድ ቆም ብሎ ያስበው። የኮሚሽኑ ውሳኔ ስንዝር መሬት ከኤርትራ ቆርሶ ለኢትዮጵያ ሰጥቶ ቢሆን ኖሮስ? ዛሬ የት ነበርን? ጋጠወጡ ወንበዴ ሸአብያ እንደገና ጦርነት ውስጥ ይማግደን ነበር። በአጭሩ መሬት ከኛ እንጂ ከኤርትራ አለመወሰዱ ኢትዮጵያ ባሳየችው ሆደ ሰፊነት ለአለም ሰላምና የህግ የበላይነት በአደረገችው አስተዋጽኦ አድናቆ ትእያተረፈች ነው። ይህ ሆደ ሰፊነት ጦርነት ለመቀስቀስ ቅንጣት ሰበብ ለተነፈገው ጥጋበኛ ሸአብያ የሞት ሞት ነው እንላለን። ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በአሸናፊነት ወጣች እያልን መረባረብ የያዝነውም ይችን ሲምፐል ሎጂክ ለህዝባችን ለማስጨበጥ ነው።

**ሸዜናአ**

ሸአብያን በጋጠ ወጥና ጦር ጠማሽነት ከመጣህ ምንም ነገር የሚሆን የለም በስነስርአት ከጠየቅህ ደግሞ ምንም የማይቻል ነገር የለም ብለን ከግዛታችንም ከህዝባችንም የተወሰነውን አስረክበናል ግን...

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

ያልከው ልክ ነው። የተወሰነውን። ማለትም በይፋ ደፍሮ አፍ አውጥቶ የጠየቀውን ከሞላ ጎደል ሙሉ በሙሉ ሰጥተነዋል። ግን በሆዱ አምቆ ከያዘው የይገባኛል ጥያቄ ስንዝር መሬት አላገኘም። የኢትዮጵያ ህዝብ የማያውቀው እኮ ብዙ ነገር አለ። ዛሬ ድባቅ የተመታው የሻብያ ህገወጥ የመስፋፋት ቅዠት በባድመ፣ ጾሮና፣ ቡሬ የሚያቆም አልነበረም። በሆዱ አክሱምን፣ አድዋን፣ መቀሌንም ይከጅል እንደነበረ ተደርሶበታል። ገና ዳር ዳር ሲል ኮስተር ስላልንበትና ፊት ስለነሳነው ነገሩን ከአፉ መልሶታል። ይህ የመስፋፋት ህልሙ እዛው ሆዱ ውስጥ እንዳለ በእንጭጩ ድባቅ ተመቷል። አክሱም፣ አድዋና መቀሌ

ኢትዮጵያዊነታቸው በማያወላዳ ሁኔታ ተረጋግጦልናል። ከእንግዲህም ሊያነሳው የሚችል አይመስለንም።

ምክንያቱም ከእንግዲህ አለም አቀፉ ኮሙኒቲ የሰጠንን፣ የፈቀደልንን፣ ያጸደቀልንና የከለለልንን ድንበር ጥሶ ለአስቸግር ቢል ያስቸግረዋል። ቅርብ ምስራቅን አምሳ አመት የሚያባላውን «የተረጋገጠና አስተማማኝ ድንበር» ችግር እኛ በሁለት አመት አጠናቀነዋል። እርግጥ ዛሬ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ሚያዝያ ሰባት በሰጡት መግለጫ «ለአሰብም ሆነ ለሌላ ጉዳይ ሰላማችንንና ዴሞክራሲያችንን አሳልፈን አንሰጥም» ብለው ለአላፊ አግዳሚው ጥጋበኛ ወረራ  ልንጋለጥ የምንችልበት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ከተውናል። በዚህ መልክ በተጋለጥንበት ሁኔታ ከእንደዚህ አይነት ጥጋበኛ ወንበዴ ተጎራብቶ ለሚኖር ሰላማዊና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ይህ ዳግም ያለመወረር አለም አቀፋዊ ዋስትና እንደቀላል ነገር መታየት የለበትም። ሸአብያ አገርሽቶበት ይህንን ድንበር ከጣሰ ጠቡ ከኛ ጋር ብቻ አይሆንም። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍብዬ በጠቀስኩት ቃለ ምልልስ እንዳሉት ይህንን ካደረገ «ግጭቱ ከተመድም፣ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅትም፣ ከአውሮፓ ህብረትም ከዩናይትድ ስቴትስም ጋር የሆናል።» በማለት የሰነዘሩት የማያዳግም ዛቻ እንደቀላል ነገር መታየት የለበትም።

**ሸዜናአ**

ጀምሬው ወደነበረው ጥያቄየ ልመለስና ሰላምና በአለም አቀፍ ደረጃ የህግ የበላይነት በማያዳግም ሁኔታ ድል እንዲያደርጉ፣ ሸአብያም ስለህግና ስነስርአት ትምህርት እንዲቀስም ኢትዮጵያ በሆደ ሰፊነት ከግዛቷም ቆርሳ ከህዝቧም ቀንሳ አስረክባለች፣ የግዛት ነገር ሲነሳ ያስቀረነውን ብቻ ነው የዘረዘራችሁት፣ በዚህ ውሳኔ ስንት ኢትዮጵያውያን የዜግነት መብታቸውን እንደተነፈጉ አልተነገረም

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

በሁለተኛው ጥያቄ ልጀምር። ስንት ህዝብ እንደሄደ እኛም በውል አናውቀውም። ዞሮ ዞሮ የኢትዮጵያን ህዝብ ቆጥረን አልተረከብንም። ስለዚህ ልንጠየቅበት አንችልም። ቤቱ ይቁጠረው ብቻ ነው ማለት የሚቻለው። የዘረዘራችሁት ያስቀራችሁትን ብቻ ነው ለተባለውም መልሴ አጭር ነው። ጊዜ ለመቆጠብ ብለን ነው። ያኛውን እንዘርዝር ካልን ላድማጭም ቢሆን ጥሩ አይደለም። ከሁዳዴ ጦም ያሰለቻል።

**ሸዜናአ**

ዘርዘር ወዳሉ ጥያቄዎች እንግባ። ሰላምና የህግ የበላይነትን ለማስረገጥ ብለን አስረከብን ካላችኋቸው ግዛቶች ውስጥ ከኮሚሽኑ ሪፖርት እንዳየነው ከሆነ ብዙዎቹን በህጋዊና ሰላማዊ ዘዴ የኢትዮጵያ እንደሆኑ እንዲጸኑ ማድረግ ይቻል ነበር። ይህ ያልተሞከረው ለምንድን ነው? ሌላውን ሁሉ እንተውና ብዙ ደም በፈሰሰባቸው በቡሬ፣ ባድመና ጾረና ጉዳይ በእናንተ በኩል እንዲያውም ክህደትና አሻጥር ተፈጽሟል የሚሉ ሀሜተኞች ያሉ ይመስላል። ስለዚህ ውንጀላ ምን ይላሉ?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

እንዲህ ያለ እንቶፈንቶ የሚያናፍሱ የገበያ ግርግር ለመፍጠር የሚፈልጉ ተርታ ፖለቲከኞችና ሰላምና የህግ የበላይነት በተጎናጸፉት ድል ጋጠ ወጥነት በተከናነበው ውርደት ቆሽታቸው ያረረ የሸአብያ ወኪሎች ናቸው። በዚህ አለም አቀፋዊ የፍርድ ሸንጎ በሰላምና በህጋዊ መንገድ እስከመጨረሻዋ የላብ ጠብታ ተዋድቀናል። የኢትዮጵያን ክብር፣ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር በተደረገው ርብርቦሽ የተነሳ እንኳን ከተማና ወረዳ ቀርቶ ስንዝር መሬት ተቆርሳ ወደ ኤርትራ እንዳትወሰድ በሰላሙ የትግል መድረክ በጀግንነት ተዋድቀናል። ከኛ ጉድለትና ስንፈት የተነሳ ስንዝር መሬት አልተወሰደም። የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት በተመለከተ የኛ መመሪያ ታላቁ ንጉስ አጼ ዩሀንስ አራተኛ የተውልን መመሪያ መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቀዋል።

« ለኢትዮጵያ እንኳን ለመሬቷ ቀርቶ ለጭብጥ አፈሯም እሳሳለሁ» ነበር ያሉት። በጦሩም ሆነ በሰላሙ ፍልሚያ በጀግንነት የተሚሟትነው በዚህ መመሪያ ስለሆነ እንኳን ስንዝር መሬት ጭብጥ አፈር አላግባብ አላስረከብንም ባዮች ነን። እደግመዋለሁ። አላግባብ አላስረከብንም ባዮች ነን!

**ሽዜናአ**

ከፍ ብለው ቁምነገሩ የግዛት ስፋትና ጥበት፣ የሜትር ካሬ ጉዳይ አይደለም ሲሉ ነበር። አሁን ደግሞ እንደ አጼ ዮሃንስ ለመሬቷም ለጭብጥ አፈሯም እንጨነቃለን አሉኝ ።እንዴት ነው?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

እንዲህ አልወጣኝም!

**ሽዜናአ**

አይ ጌታዬ ይህንን እንኳን ብለውኛል። እየተቀዳን እኮ ነው።እንደገና ላሰማዎት

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

ብዬ ነበር? ዞሮ ዞሮ እሱኛው ተብሎም እንደሆነ የተባለው በሌላ ኮንቴክስት መሆን አለበት!

**ሽዜናአ**

እስቲ በቡሬ ጉዳይ እንጀምር። ቀጥለን ወደ ጾሮናና ባድመ እንገባለን። በቡሬ ግንባር ብዙ ሰው አልቋል። በዚህ ግንባር ያለውን ድንበር የሚያካልለው የ1908 ኢ.ም ውል ነው። ውሉ የሚለው ድንበሩ ከቀይ ባህር ትይዩ ወይም ፓራለል 60 ኪሎሜትር ላይ ይሆናል ነው። በመሆኑም ቡሬ ከቀይ ባህር 72 ኪሎሜትር ትይዩ ስለሆነች ቢያንስ አስራ ሁለት ኪሎሜትር ኢትዮጵያ ውስጥ ነች። ኮሚሽኑም በውሉ መሰረት መወሰን ስላለበት ቡሬ የኢትዮጵያ ነች ብሎ ወሰነ። ከዚያ በኋላ ግን ተግባሩ ተዘርዝሮ ሲሰጠው ግራ ቀኙን ሳታይ በውሎቹ አንቀጾች ብቻ እያየህ ፍረድ የተባለው ኮሚሽን ባወጣው ሰነድ በገጽ 92 እና 93 ላይ «ቡሬን በተመለከተ ለየት ያለ ሁኔታ አጋጥሞኛል» ይልና በእናንተው ጥያቄ ውሉን አሻሽዬ ቡሬን ድንበር ከተማ ማድረግ ተገደድሁ ይላል።ይህ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመ ግልጽ አሻጥር ነው እያሉ እስከማማ የሚቃጣቸው ፈትፋቾች አልጠፉም። ነገሩን እንዴት ያዩታል?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

ቡሬ ላይ ጉድ የተሰራነው በመርህ ጉዳይ ነው! አሻጥር አይደለም። ፕሪንሲፕል ወዳጄ! ፕሪንስፕል! የሆነው ምንድንነው? እዚህ ላይ በ1986 ኢ.ም. የጣልያኑን የድንበር ውል አፍርሰን ይችን ከተማ የጋራ ድንበር ለማድረግ ከሸአብያ ጋር የምስጢር ውል መፈራረማችንን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲረዳልን እንፈልጋለን። ሸአብያ ለኮሚሽኑ የውሉን ቅጅ አቀረበ። እርግጥ በይፋውና እንዳኘበት ባልነው የቅኝ ግዛት ውል ጸንተን ቡሬን ማዳን እንችል ነበር። ነገር ግን ህሊናችን በመርህ ጉዳይ የሚጨነቅበት ሁኔታ ተከሰተ። በአንድ በኩል ተስፋፊ ኮሎንያሊስት ጣልያን ከአንድ ግፈኛ ፊውዳል የጦር አበጋዝ ጋር የተፈራረመችው ውል አለ። በሌላ በኩል ደግሞ የዛሬን አያርገውና የሻብያ መሪዎች አብዮታዊ ዴሞክራሲያውያን በነበሩበት ጊዜ ከኛ ጋር የተፈራረሙት ውል አለ። ሁለቱ አንድ አይደሉም ለየትኛው ቅድሚያ እንስጥ? ከመርህ አንጻር ሲታይና በሃቅ ለሃቅ እንቁም ከተባለ ለአስር አስራአምስት ኪሎሜትር ተብሎ የአብዮታውያን ቃል ሲታጠፍ አልታየንም። ምስጢሩ ይኸው ነው። የመርህ ጉዳይ ሆኖብን ነው እንጂ ሌላ ነገር ከጀርባው የለውም።

**ሸዜናአ**

እዚህ ላይ ለአስር አስራ አምስት ኪሎሜትር ብለን ይላሉ ከፍ ብለው ታላቁ አጼ ዩሀንስ አራተኛ እንኳን ለመሬቷ ለአፈሩም እሳሳለሁ ያሉት የኛ ቋሚ መመሪያ ነው ብለው ያሉ መስሎኝ!??

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

እሱኛው የተባለው በሌላ ኮንቴክስት ነው!

**ሸዜናአ**

ወደ መሃል ግንባር እንምጣ። በጾሮናና አካባቢው ጉዳይ። አንዳንድ ሰው አጠቃላይ አካሄዱን እያየ ብዙ ትግል የተደረገባቸውንና ብዙ ደም የፈሰሰባቸውን አካባቢዎች ሆን ብላችሁ ያስረከባችሁ ይመስላል እያለ እስከማማት ይቃጣዋል። እዚህም ላይ ኮሚሽኑ በሰነዱ ገጽ50 ላይ በ1900 አም የቅኝ ግዛቱ ውሉ መሰረት ጾሮናና ፎርቶ ኮዶማ በግልጽ የኢትዮጵያ ናቸው ብየ ተከራክሬያለሁ ግን የኢትዮጵያ መንግስት የኛ አይደሉም ብሎ በጽሁፍ ባስገባው ማመልከቻ (ፕሊዲነግ) መሰረት አሁንም ከተሰጠው ማንዴት ውጭ በእናንተ ግፊት የቅኝ ግዛት ውሉን ሽሮ እነዚን ግዛቶች ኤርትራ ውስጥ የሚያስገባ አዲስ ካርታ ለማጽደቅ ተገድጃለሁ ይላል። ይኸ ክህደትና አሻጥር ነው እስከማለት የደፈሩ አንዳንድ ወገኖች አልጠፉም። ጉዳዩን እንዴት ያዩታል?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

በነጾሮና ጉዳይ ያስጠቃን ሃቀኝነት ነው። የኛ እንኳን ባይሆን  የኢትዮጵያ ህዝብ ሀቀኝነት። ጾሮናን ብንወስድ ከዚህ ከሃቀኛ ህዝባችን በኩል ሊያስከትልብን የሚችለው ትዝብት አሰጋን። ቁጣውን ፈራን። ከፍ ብየ እንዳልኩት ኢትዮጵያ የራሷንም የማታስነካና የሰውም የማትፈልግ ጨዋ አገር ነች። ይኸ ማለት ህዝባችን ጨዋና አስተዋይ የሰው የማይፈልግ ሀቀኝነት የሚያጠቃው ታላቅ ህዝብ ነው ማለት ነው። እርግጥ በኮሎኒው ውል መሰረት እነጾሮና የኢትዮጵያ ናቸው። ግን ሙግት ላይ እንዳለን ከየት ማንና እንዴት እንደነዛው የማይታወቅ አንድ ጭምጭምታ ተሰማ። ይኸ ጭምጭምታ ምንድን ነው? አጼ ምኒሊክ ጾሮናንና አካባቢዋን ለጣልያን የለቀቁበት ለጊዜው የትና በማን እጅ እንዳለ የማይታወቅ ጥብቅ ምስጢር የሚል እነጾሮናን ለጣልያን የሚሰጥ ውል አለ የሚል ነበር። ሳይታሰብ ከባድ ፈተና ላይ ወደቅን።

ምንም ምስጢርና በጭምጭምታ ደረጃ ቢሆን፣ ምንም እንኳን ለጊዜው የት እንዳለና ዝርዝር ይዘቱ ባይታወቅም ይህ ታላቁ ንጉሰ ነገስት ምኒልክ በክቡር ብእራቸው በኢትዮጵያ ስም ፈረሙት የተባለ ክቡር ሰነድ ባልተጠበቀ ሁኔታ ሸአብያ እጅ ቢወድቅስ ? ሸአብያ ይፋ ቢያደርገውስ? ልብ በል እንግዲህ። ልክ እንደ ቡሬው ሁኔታ እዚህም ላይ የህሊና ጭንቀት ሊመጣ ነው።

ይህን ክቡር ሰነድ በምስጢር ይዘን ጾሮናንና አካባቢዋን በሸወዳ ለኢትዮጵያ እናስቀር? ወይስ የእምየ ምኒልክና የኢትዮጵያ ቃል የማይታጠፍ ክቡር ነገር ነው ብለን ጾሮናንና አካባቢዋን ማንም ሳይጠይቀን ተሽቀዳድመንና ከኮሚሽኑ ተሚግተን እናስረክብ? ይህንን ከማድረግ ይልቅ ዛሬ ጾሮናን በዚህ መልክ አስቀርተን ነገ ይህ ሰነድ ቢገኝና በሆነ ዘዴና ተንኮል ይፋ ቢወጣ  ጨዋውና የሰው የማይሻው የኢትዮጵያ ህዝብ መሪዎቼ አሳፈሩኝ ብሎ አንገቱን የሚደፋበት ሁኔታ እንደማይከሰት ማረጋገጫችን ምንድን ነው! ይህ ጨዋና ሃቀኛ ህዝብ በስሜ አጭበረበራችሁ፣ የማይገባንን ወሰዳችሁ ብሎ በቁጣ ቢነሳ የሚቋቋመው ማነው!? ይህንን ሁሉ መዘዝ ፈርተን ነው እነ ጾሮናን ከኮሚሽኑ ተሚግተን ለኤርትራ ያስረከብነው። ሌላ ምስጢርም አሻጥርም የለውም። ያስጠቃን የህዝባችን ሃቀኛነት ነው።

**ሽዜናአ**

አይ! ከፍ ብለው አጼ ምኒሊክን ጸረ ህዝብ ፊውዳል የጦር አበጋዝ ብለው ወረፍ አርገዋቸው ነበር አሁን ደግሞ የንጉሰነገስት የእምየ ምኒልክ ቃል ክቡር ምናምን ይላሉ...

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

እሱኛው የተባለው በሌላ ኮንቴክስት ነው!

**ሽዜናአ**

የባድመም ጉዳይ እጅግ የሚያስገርም ነው። አብዛኛው ሰው ብዙ ፈረንጆችን ጨምሮ ባድመ ሄዳለች ይላል። እዚህ ላይ ሰሞኑን እንኳዋን የአካባቢው ኑዋሮዎች ዘላለማችንን ኢትዮጵያዊ ነበርን። አሁንም ኢትዮጵያዊ ነን። ኤርትራዊ ሆነን የምናውቅበት ወቅት የለም እንደሚሉ የአለም የዜና አውታሮች ሳይቀሩ እየዘገቡ ነው። እናንተም እኛም ስንል የነበረው ይቺ አካባቢ በኮሎኒውም ጊዜ በንጉሱም፣ በደርግም በእናንተም ዘመን ከኢትዮጵያ አስተዳደር ስር ነበረች። አሁን ኮሚሽኑ በሰነዱ ፓራግራፍ 5.92 ላይ የኢትዮጵያ መንግስት ባድመን ለማስተዳደሩ አሳማኝ መረጃ ባለመቅረቡ ይህንን አካባቢ ለኤርትራ ከመስጠት ሌላ አማራጭ አላገኘሁም ይላል። ጨርሶ ሊገባ የማይችል ነገር ነው። ማስረጃ ማቅረብ ተስኖዋቸው ሳይሆን ክህደት አሻጥር ምናምን እያለ የሚያማ አልጠፋም...

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

ባድመን ጉድ የሆነው በቅን ዝንጋታ ነው። አክሱምን፣ መቀሌን፣ደሴን፣ ጎንደርን፣ አዲስ አበባን ወዘተ ለማስተዳደራችሁ ሰነድ አምጡ ሊባል እንደማይቻል ሁሉ ለባድመም መረጃ ያስፈ ል ጋል ብለን ጨርሶ አልገመትንም ነበር። ከሆነ በኋላ ስናስበው ግን በአካባቢው የይገባኛል ውዝግብ ከተነሳ አይቀርና የኛ ነው ካልን ዘንዳ መረጃዎቻችንን ማሰናዳት ነበረብን። ነጥቡን ዘነጋነው። ለክፋት ሳይሆን ቅን ዝንጋታ ያልኩት ለዚህ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ሌላ መረሳት የሌለበት ቁም ነገር አለ። ወቅቱ በአብዮታዊ ዴሞክራሲዊ አመራር ካፒታሊዝምን ለመገንባት የርብርቦሽ ጥሪ የተላለፈበትና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የተባለ ካአጣዳፊነትም አልፎ አዋካቢ ሊባል የሚችል ተግባር ላይ የተሰማራንበት ወቅት ነው። በሱ ስንዋከብ ባድመን ዘነጋናት !

**ሽዜናአ**

ድህነት ቅነሳ ድህነት ቅነሳ ትላላችሁ እንጂ አሁን እኮ ኢያያዛችሁ ከድህነት ይልቅ ድሆችን የመቀነስ ስትራቴጂ ይመስላል። አንዳንዱ እንዲያውም በአብዛኛው ድሃ ገበሬ የሆኑ ከመቶ ሽህ በላይ ዜጎችን በአንድ ጊዜ ወደ ኤርትራ እንዲዛወሩ ማድረግ በዚያው ልክ በኢትዮጵያ የድሆችን ቁጥር እንዲያሽቆለቁል ማድረግ ነው እያለ ያሾፋል

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

(የማሽላ አይነት ሳቅ ይተናነቃቸዋል) ነገሩን በዚህ መልክ አላየነውም። ሊያስኬድ ይችላል። በበኩላችን ግን በዚህ ዜጎችን ለኤርትራ በማስረከብ ጉዳይ የምንከተለው ሌላ ረቂቅ ስትራቴጂ ነው።

**ሽዜና**

ምን ረቂቅ ስትራቴጂ ነው ትንሽ ቢያብራሩልን?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

በሙቶ ሽህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን በዜግነት ቅየራ ስም ኤርትራ ውስጥ አሰርገ በማስገባት የተገንጣይ አፋሮችንና ኩናማዎችን ትግል የማጎልበት እቅድ አለ። በወዲህ ጀብሃና ሌሎች ዴሞክራት ኤርትራውያን ተቃዋሚዎች አሉ። ሰራዬ የነራስ አብርሃ አገር በሃማሴኖች ላይ ልቡ የሸፈተ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። አከለ ጉዛይም አከለ ጉዛይ ነው። በዚህ ላይ አክራሪው እስላም አለ። ሸአብያ ልብ ከገዛና ከጨመተ ማንም አይነካውም። ቢጋጠወጥነት እቀጥላለሁ ካለ ከኛ በፈለሱት ዜጎች የተጠናከረው ተገንጣይ ሃይል እንዲያስቸግረው እናደርጋለን። ከኛ ከገጠመ ደግሞ ከዚህ በፊት የአፋር ተገንጣዮችን ትግል አብረን እንደመታነው «ኢትዮጵያዊነት» እያሉ በጎረቤት አገራችን ኤርትራ አለመረጋጋት ለመፍጠር የሚሞከሩትን «ጸረ ህዝብና ጸረ ሰላም» እያልን ከሸአብያ ጋር አብረን እንመታለን። በዚህ ሂደት ሸኣብያ አገዛዝ ስር ስንፈልግ የምናፈነዳው ስንፈልግ የምናስተኛው ቦምብ ቀበርን ማለት ነው ።የሃገራችን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች መጨነቅ የለባቸውም። ሰራው...እ... ይቅርታ ከአፌ አመለጠኝ ...ይቅርታ ስራው እየተሰራ ነው!!

**ሽዜናእ**

ታዲያ እንዲህ ከሆነ ለስትራቴጂው ውጤታማነት ሲባል ከባድመም፤ ከጾሮናም አልፎ ከትግራይም፤ ከጎንደርም ሰፋፊ ግዛትና ህዝብ መስጠት ምን ነበረበት፡

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

ስማ ወዳጄ! የኢትዮጵያ ህዝብ ድሃ ህዝብ ነው። ድሃ ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን መንፈስ ድሃ ነው። ስለዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ መንፈሰ ድሃ ህዝብ ነው። አርቆ አስተዋይነት ያንሰዋል። የዛሬውን የራሱን እንጂ ነገ ይቺ አገር የት ናት? የትስ መሆን አለባት? ብሎ ለማስብ ያልታደለ ህዝብ ነው። ዛሬ ከሰጠነው አልፈን ሌሎች ግዛቶች ብናስረክብ ኖሮ አይገባውም ነበር። ይነሳብናል ብለን ፈራን።

**ሽዜናአ**

ግን እኮ ቅድም ስለኢትዮጵያ ህዝብ ታላቅነት ጨዋነትና አርቆ አስተዋይነት ብዙ....

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

ኣሱኛ'ው የተባለው በሌላ ኮንቴክስት ነው

**ሽዜናእ**

ጊዜዎትን ብዙ አቃጠልኩ። ወደ ጥያቄዎቼ መጨረሻ ልግባ። አሁን የባድመ ጉዳይ መልሶ አከራካሪ እየሆነ ነው። ሁለቱም ወገኖች ባድመ ለኛ ተበይናለች ይላሉ። ጨርሶ የማይገባ ነገር ሆኗል ለብዙው። ሀ ብሎ ጦርነቱ የተጀመረበትን ቦታ ኮሚሽኑስ ቢሆን እንዴት ቁርጥ ያለ ውሳኔ ሳይሰጥበት ቀረ ባድመ የኛ ነች ወይስ ተወስዳለች።

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

*መወሰዱን ተወስዳለች። ቁርጥ ያለ ውሳኔ ይሰጥ ብለን ሸንጣችንን ገትረን አልተከራከርንም። ጉዳዩ መድበስበሱ ለኛ የሚያመች ሁኔታ ይፈጥራል። በስፍራው የተቀበሩ ፈንጂዎች ጸድተው ችካል እየተደረገ ድንበር እስከንካለል ድረስ ቢያንስ አንድ አመት ይወስዳል። እስከዚያ አሸንፈናል፣ ባድመ የኛ ነች እያልን ጊዜ እንገዛለን ማለት ነው።*

*በዚህ ጊዜ ውስጥ የህዝብ ቁጣ እየገነፈለ ከመጣና በተለይ ደግሞ ሰራዊቱ ተከፍሎ አመጽ አንስቶ መቋቋም የማንችለው አስጊ ሁኔታ ውስጥ ከወደቅን በባድመ ጉዳይ ከኢትዮጵያ በማበር እንደገና ከሸኣብያ ሰራዊት እንፋለማለን። ፈረንጆች «ባክ ቱ ሰኩዌር ዋን» እንደሚሉት መሆኑ ነው። የህዝቡ ተቃውሞ የሚባለው የተቃዋሚ ተብየዎች ፍሬቢስ ጫጫታ ከሆነ ደግሞ ሁኔታዎች እንደተመቻቹ « የባድመ ጉዳይ አለመግባባት ነበር። ቅን ስህተት ተደርጓል። እውነትም አለምአቀፉ ኮሙኒቲ የወሰነው ለካ ለሸአብያ ኖሯል" ብለን ሃቁን ይፋ እናደርጋለን። የባድመ ጉዳይ ብዙ ስሜት ሊነካ የሚችል ጉዳይ በመሆኑ ሰራዊቱ ተከፍሎ የሆነው ክፍል በኛ ላይ ሊነሳ የሚችልበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። ያኔ ደግሞ በዚሁ በባድመ ጉዳይ «ያገባኛል» ማለቱ ከማይቀረው ከሸአብያ ወግነን ለአለም አቀፍ የህግ የበላይነት አንገዛም የሚሉትን ጋጠወጥ ኢትዮጵያውያን ልንወጋ የምንችልበት ሁኔታ ይከሰታል ማለትነው።*

**ሽዜናኦ**

*ግጭትና ትርምስ አይቀሬ ነዋ በዚህ ሁኔታ ?*

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

*መቅረቱን አይቀርም። እሱ አይቀሬ ነው። ከወዲሁ ገና ያልለየለት ነገር ቢኖር እኛ ከማን ወግነን ማንን እንደምንፋለም ብቻ ነው።*

**ሽዜናአ**

ከወዲሁ ወግነዋል፣ ሰዎቹ በኤርትራ ቀልድ የለም ባዮች ናቸው የሚባለው ዝም ብሎ መሆኑ ነዋ?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

*ሰማ ወዳጄ! እኛ በኢትዮጵያ፣ በኤርትራ በምንትስ ቀልድ የለም አንልም። ይህ የዘረኞች አካሄድ ነው። እኛ በደፈናው ቀልድ የለም ነው የምንለው። የተዋጣለትና ቋሚ ወገናዊነት ብሎ ነገር የለንም። ከእናቶቻችን አገር ወግነን የአባቶቻችንን አገር፣ ከአባቶቻችን ወግነን የአናቶቻችንን አገር፣ ካማቾቻችን ወግነን ምራቶቻችንን፣ ካከስቶቻችን ወግነን አጎቶቻችንን እንደአመጣጡ ተራ በተራ ተፋልመናል። ወደ ፊትም ከዚህ የተለየ ነገር አይኖርም። ወቅቱ ቀውጢ ወቅት ነው። ወንድም፣ እህት፣ ጓድ፣ ጓደኛን ተውና ልብህን ራሱን የማታምንበት ሁኔታ ነው ያለው።*

**ሸዜናአ**

ግን እኮ ይኽ ሁሉ ሲታይ ለተቃዋሚ ሃይሎች ደረታችሁን እንድትሰጡ እያረጋችሁ ነው?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

የትኛው ተቃዋሚ ሃይል በሃገሪቱ እኮ ተቃዋሚ ተብየ ነገር የለም።ያሰፈሰፈው ተፎካካሪ ሃይል ነው። በየብሄርህ አልነው በየብሄሩ ከተተ። በየክልልህ አልነው በየክልሉ ታጠረ። ነጻ ገበያ አልን ነጻ ገበያ አለ። ለዚህ ሁሉ «አማራጭ አምጣ» አልነው ውጭ ነፍስ ግቢ ነፍስ ሆነበት። ወቅቱ የግሎባላይዜሽን ወቅት ነው። በታሪክ አጋጣሚ እኛ ቀድመን እጅ ሰጥተናል። ተቃዋሚ ተብየው ከአሜሪካኖች አንጻር የያዘው ደጅ ጥናት «እኔ እሻልሻለሁ» የሚለው ዘፈን አይነት ነው። እንዳልኩህ ነው። የተያዘው ፉክክር እንጂ ተቃውሞ አይደለም። ዴሞክራሲ፣ ነጻ ምርጫ እያለ ጥያቄዎችን ከማንሳት አልፎ በቁም ነገሮች ላይ ከኛ የተለየ ፖሊሲ የለውም። ህዝቡን ሳይሆን መቀስቀስ የያዘው ሃያላኑን ነው። ቢበዛ ቢበዛ ከአሜሪካኖቹ «አስር አመት ብቻችሁን በልታችኋል አካፍሉ» የሚል ግፊት ሊመጣ ይችላል። ገፍቶ ከመጣ «ጥምር መንግስት» ብለን አንዳንዱን የባህልና ስፖርት፣ የጡረታ ጉዳይ፣ የቅርሳቅርስ ሚኒስትር እያልን ስንሾመው እነሱም ይኽ ይበቃሃል ይሉታል ተቃዋሚ ተብየውም አልፎ መጠየቅ ይፈራል። በዚህ በኩል ምንም ስጋት የለንም።

**ሸዜናአ**

ቢሆንም ችግር ላይ ያላችሁ ይመስላል። ይህ ሁሉ ረቂቅ የተባለ ስትራቴጂና ስሌት ድንገት አንዲት ቦታ አንድ ቀን ስቶ አደጋ ላይ የመውደቃችሁን ሁኔታ አስባችሁበት ታውቃላችሁ ወይ አንዲያው ለነገሩ ?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

ጨዋታው እስከ አሁን ሰርቷል። ግን ደግሞ ከእለት እለት አደገኛ እየሆነ መምጣቱም የዚያኑ ያህል ግልጽ ነው። ልጆቻችንን ሚስቶቻችንን ንብረታችንን አሸሽናል። አንደነ መንግስቱ ሃይለማርያም በትነነው እንሄዳለን። ከዚያ የዘረፍነውን ሲሳይ እያጣጣምን ትርምሱን ከሩቅ መታዘብ ነው። በበኩሌ ዝም ብየ አልቀመጥም። ቢያንስ አንድ መጽሀፍ የመጻፍ ፍልጎት አለኝ። ሰነዶቹ ተጠራቀመው ሁነኛ ቦታ ተቀምጠዋል። አርእስቱ ሳይቀር ተሰናድቷል።

**ሸዜናአ**

መጭውን መጽሃፍዎትን ማን ሊሉት አስበዋል?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

አዲስ አበባንም፣ መቀሌንም፣ አዲግራትንም፣ነቀምቴንም፣ ደሴንም፣ ጎንደርንም፣ ሀረርንም፣ ጅጅጋንም፣ አዋሳንም፣ እታች ሞያሌን እንኳን ሳይቀር ተቀድሜያለሁ

**ሸዜናአ**

ጥያቄየን አልጨበጡልኝም መሰል ልድገመው። የመጽሃፍዎን አርእስት ምን ሊሉት አስበዋል?

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

የኛ ሰው በባድመ!!

**ሽዜናአ**

አቤት??!!

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

አስረግጠህ ሰምተሀኛል!!

**ሽዜናኣ**

ይቅርታ ሳላስበው አምልጦኝ ነው

**ቀንደኛ ባለስልጣኑ**

እሱን ተወው። ያመለጠው አምልጦታል። ለማንኛውም ለዛሬ እዚህ ላይ ይብቃን። አመሰግናለሁ።

**ሽዜናአ**

እኔም አመሰግናለሁ። እግዜር ይስጥልኝ።